# ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## አሸናፊ ቁጥሮችን ማግኘት:

የአሸናፊ ቁጥሮችን መረጃ ከየት አገኛለሁ?

ዕኩለ-ቀን እና ምሽት ላይ የሚወጡ ዕጣዎችን በዲሲ ሎተሪ ድህረገፅ ላይ መመልከት ይቻላል። ተጫዋቾች የዲሲ ሎተሪን ሎቶ መስመር (Lott Line) በ(202) 678-3333 ደውለው አሸናፊ ቁጥሮችን መጠየቅ እና አሸናፊ ቁጥሮቹ ወደሞባይል ስልካቸው ሊተላለፍላቸው የሚያስችል አማራጭም አላቸው። አሸናፊ ቁጥሮች በዲሲ ሎተሪ ሶሻል ሚዲያ ገፆች፣ ትዊተር (Twitter (@dclottery) እና ፌስቡክ (Facebook) ጨምሮ፣ ይለጠፋሉ እንዲሁም በዲሲ ሎተሪ መሸጫ ቦታዎች ይገኛል።

## ሽልማቱ ይገባኛል ማለት:

የዲሲ ሎተሪ ሽልማትን እንዴት ይገባኛል ለማለት እችላለሁ?

ሽልማትዎን ለመውሰድ ቀላል ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘረው መረጃ የተለያዩ የሽልማት ደረጃዎችን የት ይገባኛል ለማለት እንደሚችሉ ይዘረዝራል።.

| መጠን | የሚከፈልበት ቦታ |
|---|---|
| እስከ $600 | በማንኛውም የሎተሪ ቢሮ እና የልግስና ጨዋታዎች ድርጅት<br>የሎተሪ ቢሮ እና የልግስና ጨዋታዎች ሽልማት ማዕከል |
| ከ$600 በላይ እና እስከ $5,000 | የሎተሪ ቢሮ እና የልግስና ጨዋታዎች ሽልማት ማዕከል<br>Agent plus locations |
| የሽልማቱ መጠን ከ$5,000 በላይ | የሎተሪ ቢሮ እና የልግስና ጨዋታዎች ሽልማት ማዕከል |

የሎተሪ ቢሮ እና የልግስና ጨዋታዎች የሚገኙበት አድራሻ በ2235 Shannon Place, SE Washington, DC 20020 ነው። የሽማት ማዕከሉ የስራ ሰዓት ከ8:00 a.m. እስከ 4:30 p.m.፣ ከሰኞ እስከ አርብ ነው። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር (202) 645-8000 እባክዎን ይደውሉ።

## የአሸናፊ ቲኬቱን ከጠፋብኝ ምን ይሆናል?

የዲሲ ሎተሪ ለጠፉ ወይም ለተሰረቁ ቲኬቶች ኃላፊነት አይወስድም። በቲኬትዎ ጀርባ ላይ በእስከሪብቶ መፈረም እና አስፈላጊውን የጥንቃቄ ሃላፊነትን ይውሰዱ። አንድ ጊዜ ከተፈረመ ቲኬቱ በእጁ የሆነ ማንኛውም ግለሰብ የይገባኛል ጥያቄ ፋይል ማድረግ ይችላል።

## አከፋፋይ ሺያጭ ይሁኑ:

የዲሲ ሎተሪ አከፋፋይ ሺያጭ እንዴት መሆን እችላለሁ?

የዲሲ ሎተሪ አከፋፋይ ሺያጭ መሆን ቀላል ሂደት ያለው እና ለበርካታ የንግድ ዓይነቶች ፈቃድ ያለው አከፋፋይ ሺያጭ እንዲሆኑ፣ ሎተሪው ማበረታቻዎችን ይሰጣል። የንግድ ቦታዎ ትርፋማ የሆነ የሎተሪ ማከፋፈያ ሊሆን ይችላል። የዲሲ ሎተሪ አከፋፋይ ሺያጭ ለመሆን የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ዛሬውኑ በ202-645-8041 ወይም በኢሜል OLCG.licensing@dc.gov ያነጋግሩን።

## የሎተሪ ማጭበርበርን እና ማወናበጃዎችን ሪፖርት ማድረግ:

የሎተሪ ማጭበርበርን እና ማወናበጃዎችን እንዴት ሪፖርት አደርጋለሁ?

"የሎተሪ ቲኬት ካልገዙ፣ ሽልማት ማሸነፍ አይችሉም"!!
"ሕጋዊነት ያላቸው ሎተሪዎች፣ ተጨዋቹ ያሸነፈውን ሽልማት ለማግኘት በቅድሚያ የሚከፈል ገንዘብ በጭራሽ አይጠየቅም"

ከላይ የተጠቀሰውን ማስታወሻን በአእምሮዎ ከያዙ፣ የሎተሪ ማጭበርበር ሰለባ ሊሆኑ በጭራሽ አይችሉም። ከአጭበርባሪ አካል የስልክ ጥሪ፣ ደብዳቤ ወይም በሌላ መገናኛ ሁኔታ ከደረሰዎት፣ የፌደራል ንግድ ኮሚሽንን (Federal Trade Commission) ያሳውቁ። እኛንም (በቢሮ) ስልክ ቁጥራችን 202-645-8080 ወይም በአጣዳፊ መስመራችን (Hotline Number) 202-645-9009 በመደወል የማወናበድ ወይም ከሌሎች የደህንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሪፖርት እንዲያደርጉ እናበረታታለን።

ስለዚህ የበለጠ ማወቅ Sweepstakes and Lottery Scams

## ኃላፊነት ወስደው ይጫወቱ:

የቁማርተኝነት ችግር ላለው ሰው እርዳታ እንዴት አገኛለሁ?

ሎተሪ መጫወት "አዝናኝ ኢንቨስትመንት፣ በተቃርኖ፤ የገንዘብ ኢንቨስትመንት" ("fun investment vs. a financial investment,") በመሆኑ እና እንደ ንግድ እና የባለሙያ ማህበረሰብ አባልነት፣ ለተጫዋቾቹ እና ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪዎች የዲሲ ሎተሪ ያለበትን የማህበራዊ ኃላፊነት ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል። የዲሲ ሎተሪ "ኃላፊነት በመውሰድ መጫወት" ("Play Responsibly") በሚለው ፕሮግራም፣ የቁማርተኝነት ባሕሪን እንደ ሱስ የሚያሳዩ ወይም ወደዚህ ዓይነቱ ድርጊት አዝማሚያ ያላቸውን የእርዳታ መስመር እና የመመሪያት አገልግሎት ይሰጣል።

እርስዎ ወይም ሌላ ሰው የቁማርተኝነት ችግር እንዳለው ካወቁ፣ የብሄራዊ ካውንስል፣ በቁማርተኝነት ችግር (National Council on Problem Gambling) የእርዳታ መስመርን 1-800-522-4700 ይደውሉ።

ምን ያህል ነው በቂ የሚባለው ወይም ምን ያህል ነው ብዙ? መጠንዎ ምን ያህል ነው?
www.ncpgambling.org
www.gamblersanonymous.org

## ቲኬቱን በቅድሚያ መግዛት እችላለሁ?

አዎን። የDC-2፣ DC-3፣ DC-4፣ እና DC-5 እስከ ሰባት ተከታታይ ቀናት በእኩለ ቀን እና በማታ የሚወጡ ቲኬቶች በቅድሚያ መግዛት ይቻላል። POWERBALL®፣ Mega Millions®፣ እና Lucky for Life® ከ1፣2፣4፣6፣8፣10፣ 12፣14፣16፣18፣ እና 20 ተካታታይ መውጫ ቀናቶች በፊት ቲኬቶችን መግዛት ይቻላል።

## ከሎተሪ የተገኘው ገንዘብ ወዴት ይውላል?

ከዲሲ ሎተሪ የተገኘው ገንዘብ ለጨዋታዎች እና የሎተሪ ፈቃዶች ቁጥጥር የከንውን ወጪዎች፣ አስተዳደራዊ ስራዎች፣ እና ካፒታል ወጪዎች ይውላል። አብዛኛው ገንዘብ ወደ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ አጠቃላይ የተሰበሰበ ገንዘብ (General Fund) ይተላለፋል። ተጨማሪ መረጃ በዲሲ ሎተሪ ዓመታዊ ሪፖርት በdclottery.com ይገኛል።

## የሎተሪ ሽልማቶች ታክስ ይቆረጥባቸዋልን?

በሌላ የሥልጣን ክልል ላሉ ነዋሪዎች የሚከፈሉ የዲሲ ሎተሪ ሽልማቶች፣ የሚመለከተው የሥልጣን ክልል የሚጠይቀውን መስፈርቶች ተከትሎ፣ የፌደራል እና ስቴት ታክሶች እና የአካባቢው ታክስ ተገዢ ሊሆን ይችላሉ። ከ$600 በላይ የሆኑ አሸናፊ ሎተሪዎች፣ በፌደራል ደንቦች መሠረት ለአገር ውስጥ ገቢ የገቢ ስብሰባ አገልግሎት ሪፖርት ይደረጋሉ።

## የIRS ቅፅ W-2Gን ሌላ ቅጂ እንዴት አገኛለሁ?

የዲሲ ሎተሪ ከ$600.00 በላይ የሆነ የሎተሬ አሸናፊ ቼክ ሲልክ በአባሪነት የW-2Gን ቅፅ አብሮ ይልካል። የቅፁን ተጨማሪ ቅጂ ለማግኘት፣ በ202-645-8065 ይደውሉልንና የIRS ቅፅ W-2Gን ለማግኘት እንደጠየቁ ያስረዱ፤ የዲሲ የገንዘብ አገልግሎት የሎተሪ ቢሮ ጥያቄዎትን ያስተናግዳል።